ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

ስትራቴጂያዊ የኃይል ማመንጫዎች ጥናት

የኤሌክትሪክ ኃይል ለአንድ አገር እድገትና ብልጽግና መሠረት ናቸው ከሚባሉ ጉዳዮች ግንባርቀደም ነው።ኢትዮጵያ ከተለያዩ አማራጮች የኤሌክትሪክ ኃይል የማምረት አቅሟን እያሳደገች የምትገኘውም ኤሌክትሪክ ለመጪው ዘመን እድገቷ ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን በማመን ነው። የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የአገሪቱን የኃይል አቅርቦት እንዲያሳድግ ኃላፊነት የተጣለበት መንግሥታዊ የልማት ድርጅት ነው። ተቋሙ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ኃይል የማቅረብ ሥራውን በብቃት ሲወጣ የቆየ ሲሆን በቀጣይ የተሰጠውን ተልዕኮ መወጣት የሚያስችለውን የረዥም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ እቅዶችን አዘጋጅቷል። ተቋሙ ከ25 ዓመቱ ማስተር ፕላን እየተቀዱ በሚዘጋጁ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ እቅዶቹ ዐቢይ እና ንዑስ የሥራ ተግባራትን እያከናወነ የስኬት ጉዞውን ቀጥሏል።

አቶ ማርዓለም ዓመደብርሃን ፣

አቶ ማርዓለም ዓመደብርሃን በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮርፖሬት ፕላኒንግ ዘርፍ የጀነሬሽን ስትራቴጂና የኢንቨስትመንት ክፍል ሥራ አስኪያጅ ናቸው። እሳቸው እንደሚያስረዱት፤ ተቋሙ ከተለያዩ የኃይል ምንጭ አማራጮች የኤሌክትሪክ ኃይልን ለማምረት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል። በዚሁ መሠረት የኮርፖሬት ፕላኒንግ ዘርፍ የጀነሬሽን ስትራቴጂና የኢንቨስትመንት ክፍል አስቀድሞ የኃይል አማራጮችን ይለያል፤ የአዋጭነት ጥናቶችን ያከናውናል። በመሆኑም የትኞቹ የኃይል ማመንጫ አማራጮች ቅደሚያ ይሰጣቸው? አመቺነታቸው ምን ይመስላል? መቼ፣ የት እና እንዴት ይተገበራሉ? የሚለውን ለይቶ ያስቀምጣል። ኃይልን ተደራሽ የሚያደርጉ ምን ዓይነት የኃይል ማመንጫ፣ ማከፋፈያ ጣቢያዎች እና ማስተላለፊያ መስመሮች ያስፈልጋሉ? በሚሉ ጉዳዮች ላይም ጥልቅ ጥናት ያደርጋል።

ተቋሙ ከኃይል ማመንጫ እና ማከፋፈያ ጣቢያዎች እንዲሁም ማስተላለፊያ መስመሮች ዝርጋታ አንጻር ሁሉንም አገልግሎቶች ታሳቢ በማድረግ በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ምን ዓይነት የኃይል አቅርቦት ያስፈልጋል የሚለውን ተገማች አድርጓል። ተገማች የሆነውን የኃይል ፍላጎት ለማሳካት ምን ያህል ፕሮጀክቶች ያስፈልጋሉ? የትኞቹ ኃይል ማመንጫዎች ወይም ማከፋፈያዎች፤ የት ቦታ፣ መቼ እና እንዴት ሊገነቡ ይችላሉ? በሚል የተጠኑ የኃይል ማመንጫዎች በጊዜ ቅደም ተከተል ይተገበራሉ።

እነዚህን ፕሮጀክቶች ለመተግበር ምን ያህል በጀት ያስፈልጋል? በጀቱ ከየት ይገኛል? ምን ያህል የሰው ኃይል ያስፈልጋል? የሚሉት ጥያቄዎች ሁሉ በጥናቱ መልስ ያገኛሉ። በተያያዥ አበዳሪ ተቋማት፣ የግል ባለሀብቱና መንግሥት የሚኖራቸው ሚና ይለያል። ተቋሙ ምን ዓይነት አማራጮችን ተጠቅሞ ሊያሟላቸው ይችላል የሚለው አስቀድሞ ይታወቃል።

የ25 ዓመቱን የተቋሙን እቅድ ሁሉም የተቋሙ የሥራ ዘርፎች እንዲያውቁት ተደርጎ በቦርድ ከጸደቀ በኋላ ወደ ትግበራ እንዲገባ ተደርጓል። ይህ የሃያ አምስት ዓመት እቅድ ረዥም ጊዜ የሚፈጅ በመሆኑም እስከ አስር ዓመት የሚከናወኑት የመካከለኛ ጊዜ፤ እስከ ሦስት ዓመት የሚከናወኑት ደግሞ የአጭር ጊዜ ተብለው ተቀምጠዋል።

ኢትዮጵያ ከውሃ፣ ከንፋስ፣ ከፀሐይ ከተፈጥሮ ጋዝ በቂ ኃይል ማመንጨት የሚያስችል ጸጋ እንዳላት በጥናት መረጋገጡን አቶ ማርዓለም ያስረዳሉ። እንደእርሳቸው አባባል፤ ከውሃ 45 ሺ ሜጋ ዋት ከንፋስና ከፀሐይ ከአንድ ሺ ጊጋ ዋት በላይ እንዲሁም ከጂኦተርማል 10 ሺ ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት የሚያስችል አቅም መኖሩን ይጠቅሳሉ።

ሀገሪቱ በርካታ የኃይል አማራጮችን ማልማት የሚያስችል አቅም ስላላት መንግሥት በዘርፉ ላይ የግል ባለሃብቶች የሚሳተፉበትን የተለያዩ የፖሊሲ ማሻሻያዎች አድርጓል። ይህንኑ ጉዳይ ለማሳለጥ በገንዘብ ሚኒስቴር ስር አንድ ዳይሬክቶሬትም ተቋቁሟል።

ከሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ ከከተሞች መስፋፋትና ከኢንዱስትሪዎች መገንባት ጋር ተያይዞ የኃይል ፍላጎት እያደገ መምጣቱ የዘርፉን አቅም ለማሳደግ አስቻይ ምክንያት ሆኗል። የጎረቤት አገራት ኃይል ለመግዛት እያሳዩ ያሉት ፍላጎትም ሌላው አስቻይ ምክንያት ነው።

እስከ አሁን ድረስ የግሉ ዘርፍ በሚፈለገው ልክ እንዳይሳተፍ ያደረጉ ሁኔታዎች መኖራቸውን የጠቀሱት ኃላፊው፤ በተደረጉ ማሻሻያዎች የግሉ ዘርፍ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የሕዝቡን እና የአገሪቱን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተጽዕኖ ሳይፈጠር ተሳታፊ የሚሆንበት ሁኔታ መመቻቸቱን ገልጸዋል። ይሁንና ዘርፉ ከፍተኛ ኢንቨስትመንትን የሚጠይቅ እንደመሆኑ ዓለም አቀፍ የገንዘብ አበዳሪዎች የገንዘብ ፍላጎትን በሚፈለገው ልክ የሚፈቱ ባለመሆናቸው የውጭ ምንዛሪ እጥረት የግሉ ዘርፍ ወደፊት እንዳይራመድ ማነቆ እንደሆነ አስረድተዋል። አሁን ግን መሰናክሎችን በማስወገድ በቅርብ ጊዜ የግል ዘርፎችን ወደ ሥራ የማስገባቱ ጉዳይ ይከናወናል የሚል ተስፋ እንዳለ ጠቅሰዋል።

በግልና በመንግሥት አጋርነት የሚለሙ ፕሮጀክቶች በታሰበው ልክ ላለመሄዳቸው እንደ ምክንያት የሚጠቀሱት መንግሥት ኅብረተሰቡን ለመደጎም ወይም ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት በማሰብ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያን ዝቅ ማድረጉ አምርተን በምንሸጠው ኃይል ላይ ተጽዕኖ ያሳድርብናል የሚል የባለሃብቶች ስጋት መፈጠር እና የደህንነት ጉዳዮች መሆናቸውን ሥራ አስኪያጁ አብራርተዋል። ሆኖም እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ መንግሥት ከፍተኛ ሥራ እየሠራ ነው። በሂደትም የግል ባለሃብቶች ተሳትፎ እየጨመረ የአገሪቱ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትም እያደገ እንደሚሄድ ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል።

የተቋሙ የ25 ዓመት እቅድ ከዩኤስ ኤ ኤድ በተገኘ ድጋፍ ከእንግሊዝ አማካሪዎች ጋር በመተባበር እንደተዘጋጀ የገለጹት አቶ ማርዓለም፤ እርሱን መሠረት አድርጎ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ እቅዶች ግን በራስ አቅም መዘጋጀታቸውን ገልጸዋል።

በስትራቴጂክ እቅዱ ከዚህ በፊት የተለያዩ ዓለም አቀፍ አማካሪዎች ተሳትፎ ያደርጉ እንደነበር ገልጸው፤ ተቋሙ ከተሞክሮዎች፣ ከሶፍትዌሮች እና ከሥልጠናዎች ያገኛቸውን እውቀቶች ቀምሮ በራሱ አቅም የመካከለኛና የአጭር ጊዜ እቅዶችን እያቀደ ወደ ትግበራ መግባቱን ተናግረዋል።

ፕላኒንግ ዘርፍ ስለሚገነቡ ኃይል ማመንጫ፣ ማከፋፈያ ጣቢያዎችና ማስተላለፊያ መስመሮች ዝርጋታ ብቻ ሳይሆን በጀነሬሽን ኦፕሬሽን ዘርፍ በሥራ ላይ እያሉ ለሚያጋጥሙ ችግሮች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ እቅዶችንም ያቅዳል። በዚሁ መሠረት አቅማቸውን የማሳደግ፣ መልሶ የመገንባት ወይም የመጠገን ሥራዎችን እንደሚሠራ ሥራ አስኪያጁ አቶ ማርዓለም ይገልጻሉ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል